***Journal of Afroasiatic Languages/Journal of Afroasiatic Languages, History and Culture (JAAL)***

Volume 12, Number 1, 2023

# FUNCTIONS OF MARRIAGE RITUAL IN JABI TEHINAN DISTRICT

Siraye Endalew Wobetie
(with Waltenigus Mekonnen and Desta Amare)

## Abstract

*This study was conducted on Functions of Marriage Ritual in Jabi Tehinan district, Amhara Region. Usually, marriage is a drastic transition and transformation of human's life. Because of this during Marriage different, continuous, and functional rituals are performed. In the Jabi Tehinan district child marriage is still being practiced which makes marriage transition difficult and complex. However, many rituals help couples' transition and transform this difficult childhood marriage. The rituals have the roles of accompanying the transition of marriage (highlighting), providing treatment (healing), adapting the couples to the transition (exercising the change), announcing the change of status (confirming) and strengthening the social relationships of the community. The study, in general, looked at the rituals that take place from the eve of the wedding to the honeymoon ceremony, where the main transition and change of marriage takes place. The ceremonies have different roles for brides and the community around them.*

# የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎች ሚና በጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ[1]

ሥራዩ እንዳለው ውበቴ[2]
(ከዋልተንጉሥ መኮንን[3] እና ደስታ አማረ[4] ጋር)

**አጠቃሎ**

*ይህ ጥናት የጋብቻ ሽግግር ሥርዓተ ክዋኔዎች[5] ሚናን በጃቢ ጠህናን ማህበረሰብ ይመለከታል። ጋብቻ ሰዎች ጠበቅ ያለ ለውጥ የሚያካሂዱበት የህይወት ደረጃ ሽግግር ማድረጊያ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ፣ የተለያየ ዓላማ ባላቸውና ተከታታይ በሆኑ ሥርዓተ ክዋኔዎች ታጅቦ ይከበራል። በጃቢ ጠህናን ወረዳ ደግሞ አሁንም ድረስ ጋብቻ በልጅነት እድሜ የሚፈጸም በመሆኑ ሽግግሩን ከባድና ውስብስብ ያደርገዋል። ሆኖም በጋብቻው ወቅት በሂደት በሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች አማካኝነት ተጋቢዎች ሽግግሩን አካሂደው እና ለውጡን ተቀብለው የማህበረሰቡ አካል ሲሆኑ ይስተዋላል። ይህን ተቃርኖ አስማምተው ለውጡን እንዲላመዱ በማድረግ የማህበረሰቡ ህልውና ሚዛኑን ጠብቆ እንዲቀጥል ያስቻሉ ሥርዓተ ክዋኔዎችን እና ሚናቸውን ለማሳየት ሲባል ይህ ጥናት ተካሂዷል። ጥናቱ በዋናነት የጋብቻ ሽግግር ሥርዓተ ክዋኔዎችን ሚና በጃቢ ጠህናን ማህበረሰብ ባህልና እምነት ማሳያነት መግለጽ ነው። ጥናቱ ዓይነታዊ ሲሆን መረጃዎች ከቀዳማይና ከካልአይ ምንጮች ተሰብስበዋል። ተሳትፏዊና ተሳትፏዊ ያልሆነ ምልከታ፣ ነጻ ቃለ መጠይቅ እና ተተኳሪ የቡድን ውይይት በመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴነት ጥቅም ላይ ውለዋል። መረጃው በገለጻ፣ በትረካና በትርጎማ ስልት ቀርቧል። የመረጃ ትንተናው እንደሚያሳየው በወረዳው ዋናው የጋብቻ ሽግግርና ለውጥ የሚካሄድበትን ከሰርግ ዋዜማ እስከ ጫጉላ ግላጭ ድረስ የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎችን ጥናቱ ተመልክቷል። ምሪ[6] የመፍታት፣ ሙሽራን የመፈተንና (ጥያቄ የመጠየቅ) እና ቃል የማስገባት፣ የዞረሽ ግቢ ሥነ ሥርዓቶች በሙሽሪት ቤት የሚፈጸሙ ሲሆኑ፣ የተለየ ምግብ መመገብ፣ የጫጉላ ቤት ጨዋታ፣ ሙሽራ ጠያቂ መላክ እና የጫጉላ ግላጭ ሥነ ሥርዓቶች ደግሞ በወንድ ሙሽራ ቤት የሚቀጥሉ ናቸው። እነዚህ ሥርዓተ ክዋኔዎች ለሙሽሮች እና በዙሪያቸው ላለው ማህበረሰብ የተለያዩ ሚናዎች አሏቸው። የጋብቻ ሽግግሩን የማጀብ (የማድመቅ)፣ ህክምና የመስጠት (የመፈወስ)፣ ባለጉዳይን ከሽግግሩ ጋር የማስማማት (ለውጡን የማለማመድ)፣*

1 ይህ ጥናት በፎክሎር ሶስተኛ ዲግሪ ለማግኘት እየሰራሁት ካለው ጥናት ላይ የተወሰደ ሲሆን ለዚህ መጣጥፍ በሚመጥን መልኩ ተስተካክሎ የቀረበ ነው፡፡

2 በመዳ ወላቡ ዩኒቨርስቲ፣ የአማርኛ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍ ትምህርት ክፍል መምህርት እና በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የፎክሎር ሶስተኛ ዲግሪ ዕጩ፡፡

3 በባህር ዳር ዩኒቨርስቲ የፎክሎር መምህርና ተመራማሪ (የመርምሩ አማካሪ)

4 በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ፣ ቋንቋዎችና ባህሎች አካዳሚ፣ የባህል ዘርፍ ተመራማሪ (የመርምሩ አማካሪ)

5 ሥርዓተ ክዋኔ Ritual የሚለውን የእንግሊዝኛ ቃል ወክሎ ጥቅም ላይ የዋለ ነው።

6 ምሪ ከከብት ቆዳ የሚሰራ ቀጭን ነገር ሲሆን ልጃገረዶች እስከሰርጋቸው ድረስ በወገባቸው የሚታጠቁት የልጅነት ምልክት ነው።

*የደረጃ ለውጡን የማወጅ (የማረጋገጥ) እና የማህበረሰቡን የእርስበርስ ትስስር የማጠንከር ሚናዎች እንዳሏቸው ማወቅ ተችሏል፡፡*

**ቁልፍ ቃላት፡** *ጋብቻ፣ ሽግግር፣ ለውጥ፣ ሥርዓተ ክዋኔ፣ ሚና*

## 1 መግቢያ

ይህ ጥናት "የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎች ሚና በጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ" በሚል ርዕስ የተካሄደ ነው። ጋብቻ በባህሪው ሰዎች ጠበቅ ያለ የህይወት ደረጃ ሽግግርና ለውጥ የሚያካሂዱበት ነው። ጋብቻ የተለያየ ዓላማና ተከታታይነት ባላቸው ሥርዓተ ክዋኔዎች ታጅቦ ይከበራል። በጃቢ ጠህናን ወረዳ የዚህ ጥናት መረጃ እስከተሰበሰበበት ጊዜ ድረስ በልጅነት እድሜ የሚፈጸምባቸው ሁኔታዎች በመኖራቸው ሽግግሩ ከባድና ውስብስብ ይሆናል፡፡ ሆኖም በወቅቱ በሂደት በሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች አማካኝነት ተጋቢዎች ሽግግሩን እና ለውጡን ተቀብለው የማህበረሰቡ አካል ሲሆኑ ይስተዋላል። በመሆኑም የማህበረሰቡ ህልውና ሚዛኑን ጠብቆ እንዲቀጥል ያስቻሉ ሥርዓተ ክዋኔዎችን ሚና ለማሳየትና በጉዳዩ ላይ የተካሄደ ጥናት ባለመኖሩ ያለውን ክፍተት ለማጥበብ ሲባል ይህ ጥናት ተካሂዷል። የዚህ ጥናት ዋና አላማ የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎችን ሚና በጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ ባህልና እምነት ማሳያነት መግለጽ ነው። ጥናቱ የተካሄደው በዐማራ ክልል በምዕራብ ጎጃም ዞን ውስጥ ካሉ ወረዳዎች መካከል የጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ ላይ ነው። ወረዳው የተመረጠበት ምክንያት አሁንም የልጅነት ጋብቻ ከመኖሩ ጋር ተያይዞ ተከታታይ የሆኑና ቀናትን የሚፈልጉ ሥርዓተ ክዋኔዎች ስለሚከናወኑ፤ ለተጋቢዎች ለውጥ ያላቸውን ሚና በማጥናት የማህበረሰቡን ባህል፣ እውቀትና እምነት ለማሳየት ሲባል ነው፡፡

## 2. የንድፈ ሀሳብና የጽንሰ ሀሳብ መነሻ

### 2.1 የሥርዓተ ክዋኔ ምንነትና አስፈላጊነት

ሥርዓተ ክዋኔ በእንግሊዝኛው ሪቿዋል[7] ተብሎ ለሚታወቀው ጽንሰ ሀሳብ አቻ ተደርጎ የተወሰደ ነው። የእንግሊዝኛው ቃል አመጣጥ ሪቱስ[8] እና ሪቿዋሊስ[9] ከሚሉ ሁለት የላቲን ቃላት ሲሆን ትርጉማቸውም የተለያዩ ቤተ እምነቶች ትዕዛዛት ሥነ ሥርዓታዊ ደንብ ማለት ነው። ጉዳዩ ራሱን ችሎ መጠናት የጀመረው በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ የሃይማኖትን ምንጭ በመፈለግ ሂደት እንደሆነ ይገለጻል (ሴጋል፣ 2006[10]; 399)። ጥናቱ እንደተጀመረ ሃይማኖትን እና መስዋዕትን በመያያዝ ይጠና ነበር።

7 ritual

8 ritus

9 ritualis

10 ከእንግሊዝኛ ቋንቋ የተወሰዱ ምንጮች የህትመት ዘመን እ.ኤ.አ ሲሆን ከዐማርኛ ቋንቋ የተወሰዱት ደግሞ እንደ ኢትዮጵያን አቆጣጠር ነው፡፡

መስዋዕት በሰውና በፈጣሪ መካከል ያለውን ግንኙነት ሰላማዊ ያደርገዋል ከሚል እሳቤ እንስሳትን በማረድ ለፈጣሪና በአውዱ ለተገኘው ሁሉ በማቅረብ ስርዓቱን ይከውኑት እንደነበር ይገለጻል። ከዚያም በታሪክ፣ በስነ ሰብ፣ በሃይማኖታዊ ጥናቶች፣ በስነ ማህበረሰብ እና በስነ ልቡና መስኮች መጠናቱን ቀጥሏል (ማዛማ እና አሳንቴ፣ 2009; 575-577)።

የሥርዓተ ክዋኔን ጥናት በማስተዋወቅ የመጀመሪያ እንደሆኑ የሚነገርላቸው አርኖልድ ቫን ጀኔፐ በ1909 በፈረንሳይኛ ቋንቋ ታትሞ በ1960 በእንግሊዝኛ ቋንቋ ተተርጉሞ በቀረበው መጽሐፍ ላይ እንደገለጹት ሰዎች በሥርዓተ ክዋኔ የታጀበ የደረጃ ለውጥ ለማከናወን ባለ ሶስት እርከን መዋቅሮችን (መነጠል፣ ሽግግር እና ቅልቅል) ማለፍ አለባቸው ይላሉ። ከዚህ መሰረታዊ ሀሳብ በመነሳት ጉዳዩን ያጠኑት የስነ ሰብ ተመራማሪ ቪክተር ተርነር ቀዳሚውን የጀኔፐን ሥርዓተ ክዋኔ ድራማዊ መዋቅር ያለው የማህበረሰብ ሂደት ነው ይላሉ። የሥርዓተ ክዋኔ ሂደት የማህበረሰቡ መዋቅራዊ ክፍሎች፣ የእርስ በርስ ዝምድና እና የኃይል ሁኔታ ያጠቃልላል። የሽግግር ጊዜውም ማህበራዊ ደንቦች የሚረጋገጡበት ወይም የሚለወጡበት ሊሆን ይችላል በማለት ያስረዳሉ (ተርነር፣ 1969; 95)። በተጨማሪም (ካንዳ፣ 1988; 209) ጀኔፐን ጠቅሰው እንደጻፉት ሥርዓተ ክዋኔ የነበረን ሁኔታ የመለወጥ ሂደት ብቻ ሳይሆን ለውጥን የማረጋገጥና የመጠበቅ ሂደት ጭምር እንደሆነ ይገልጻሉ። ለዚህም ዋነኛ ምሳሌዎች የሕይወት ሽግግር ሥርዓቶች ናቸው። ይህ ጥናትም ከህይወት ሽግግር ሥርዓቶች መካከል ጋብቻ ላይ አተኩሯል።

## 2.2 የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎች ሚና

የህይወት ሽግግር ሥርዓቶች ላይ ጥናት ያካሄዱ ምሁራን እንደገለጹት የአንድ ሰው ሕይወት ተከታታይ፣ ተገቢና ግልጽ የሆኑ ደረጃዎች አሉት (ኪታሃራ፣ 1974፡ 164)፡፡ እያንዳንዱ ደረጃ የማይለዋወጥና ከእያንዳንዱ ደረጃ ጋር በተገናኘ ከማህበራዊ አከባቢ ለሚመጡ ልዩ ልዩ ክስተቶች ምላሽ ለመስጠት አንዳንድ አመለካከቶችን ያዳብራል፡፡ ሆኖም አንድ ግለሰብ ወደሚቀጥለው ደረጃ ሲሸጋገር አዲስ ማህበራዊ አካባቢ እና ተጓዳኝ አመለካከቶች ያጋጥሙታል፡፡ ይህንንም በአንድ ጊዜ የድሮውን የአስተሳሰብ አመለካከቶች ጥሎ ከአዲሱ ማህበራዊ አካባቢ ጋር በቀላሉ ለመላመድ ይቸገራል ሲሉም እነሁ ምሁር አክለው አስፍረዋል፡፡

ጋብቻ ከህይወት ሽግግር ሥርዓቶች መካከል ወሳኝ ሚና ያለው ሲሆን በብዙ ባህሎችና እምነቶች የተለያዩ ሰዎች ወደ አንድነትና አብሮነት የሚሸጋገሩበት ሁነት መሆኑ ይገለጻል (የሮያል ስነሰብአዊ ተቋም፣ 1951፡ 110)። በጋብቻ ሽግግር የተለያየ ቤት ይኖሩ የነበሩ አንድ ቤት ወደ መኖር ይመጣሉ። በሂደት በመካከላቸው ያለ አስተሳሰብም ሆነ ዓላማ መቀራረብ ይኖራቸዋል ይባላል።

በኔዘርላንድ የተለመዱ ልዩ ልዩ የጋብቻ ሥነ ሥርዓቶች ላይ የተካሄደ ጥናት እንደሚያመለክተው የጋብቻ ስርዓት ዋንኛ አላማ የሚና ሽግግር ማድረግ ነው (ካልሚን፣ 2004፡ 584)። በጥናቱ ላይ ሰዎች ከፍ ባለ ድግስ በታጀበ ጋብቻ፣ በቤተ ዕምነት የሚካሄድ ጋብቻ እና በጫጉላ ሽር ሽር አማካኝነት የእወቁልን ጋብቻን በመውሰድ ለምን

በሥርዓተ ክዋኔ ታጅበው ጋብቻ እንደሚፈጽሙ አብራርተዋል። የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔ ተጋቢዎች የደረጃ ለውጥ ዝግጅትና የጥርጣሬ ስሜትን[11] በአንድ ላይ ስለሚያስተናግዱ በአንድ በኩል ዝግጁነታቸውን ለማሳየት በሌላ በኩል የሚሰማቸው ጥርጣሬ እንዲቀንስ ያግዛቸዋል። ከዚህም ባሻገር በጋብቻው በራሱ፣ በትዳር አጋራቸው እንዲሁም ከጋብቻ በኋላ የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነት በመወጣትና ባለመወጣት ዙሪያ ጥርጣሬ ይሰማቸዋል።

በተጨማሪም የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎች ተጋቢዎች በትዳራቸው እርግጠኛ እንዲሆኑ፣ [12] ከእነሱ በፊት የተጋቡ ጥንዶችን በማየት ጋብቻውን እንዲቀበሉት፣ እንዲያምኑበትና እንዲኖሩበት ያግዛሉ፡፡ በሥርዓተ ክዋኔው አማካኝነት የሚታወጀው የሚና ሽግግር የማህበረሰቡን ደንብ ከማረጋገጥም ባሻገር እውቅና ለሚሰጠው ማህበረሰብም እንደ ማበረታቻ ነው።

## 2.3 ጋብቻ፣ ሽግግር እና ለውጥ

ሽግግር (ሊሚናሊቲ) አንድ ሰው በሁለት የማንነት ግንባታዎች መካከል ሆኖ የሚገጥመው የለውጥ ሂደት ነው (ጀኔፕ፣ 1960፡ 2)። ጀኔፕ አክለውም አንድ ሰው አንድ የደረጃ ለውጥ ሲያደርግ መነጠል፣ ሽግግር እና ቅልቅል በተባሉ የሥርዓተ ክዋኔ መዋቅሮች ያልፋል ይላሉ። ባለጉዳዩ የታሰበውን የደረጃ ለውጥ ለማድረግ በመጀመሪያ ከራሱ ማንነትም ሆነ ከማህበረሰቡ ሁለንተናዊ ሁኔታ ይነጠላል። ከዚያም ዋናውን ሽግግር አድርጎ በመጨረሻ አዲሱን ሚና እና ደረጃ ይዞ ወደ ማህበረሰቡ ይቀላቀላል የሚል መሰረተ ሀሳብ አላቸው።

ዘመናዊ ጥናቶች ሶስቱንም የሥርዓተ ክዋኔ መዋቅሮች አንድ ላይ ከማጥናት ይልቅ ነጣጥሎ ወደመመርመር ያነጣጠሩ ይመስላሉ፡፡ በተለይም የሽግግር ጽንሰ ሀሳብ ከተለያዩ አንጻሮች ማጥናት እንደሚቻል (ቶማሰን፣ 2009፡ 17) ከቦታና ከጊዜ አንጻር በማጥናት አሳይተዋል፡፡ ይህ ጥናትም ጋብቻን እንደ ሽግግር በመውሰድ በወቅቱ የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎችን ያጠና ሲሆን ለዚህም በጋብቻ ወቅት የመካከለኛው (የሽግግሩ) ሁኔታ የሚጀምረው ተጋቢዎች ከማህበረሰቡም ሆነ ከጊዜ ውጭ ከሚሆኑበት ከመነጠል ጀምሮ ነው ከሚለው (ፔንቲካናነን፣ 1979: 156) ሀሳብ በመነሳት ነው፡፡

ጋብቻ ተጋቢዎች ለአዲስ ፍሬ የሚያበቃ ወሳኝ የሽግግር ሁነት መሆኑ ይገለጻል። ሽግግር በባህሪው በአንድ በኩል አሙለጭላጭ/ አንሸራታች፤ በሌላ በኩል አቅም የሚያመነጭ መልካም አጋጣሚ ተደርጎ ይወሰዳል (ተርነር፣ 1967፡ 37) ። አክለውም በሽግግር ወቅት ያለ ባለጉዳይን ሌሚን፣[13] ሁኔታውን ደግሞ መሃል/መካከል[14] ይሉታል።

ከሽግግር ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ጽንሰ ሀሳብ ለውጥ ነው። የነበረን ሁኔታ የሚቀይርና ጠበቅ ያለ፣ ግላዊ እና ማህበራዊ የሕይወት ደረጃዎችን የማለፍ ሂደት መሆኑ

---

11 Status Preparation and Uncertainty

12 Behavioral Confirmation

13 limen

14 betwixt and between'

ይገለጻል (ካንዳ, 1988፡ 206)። በተጨማሪም ለውጥ የነበረን፣ የረጋን የመዋቅር ሁኔታ የማፍረስ፣ ለተለያዩ አዳዲስ ሁኔታዎች የማጋለጥ፣ እንደገና ለአዲስ የረጋ የመዋቅር ሁኔታ የማብቃት ሂደት እንደሆነ ካንዳን አክለው ገልጸዋል።

ለውጥ በሰው ልጅ የሕይወት ዘመን እና የእድገት ሂደት የሚጠበቁ እንደ ወሊድ፣ ለአካለ መጠን (ለአቅመ ሔዋን/ አዳም) መድረስ፣ ጋብቻ፣ ሽምግልና እና ሞት እንዲሁም በማይጠበቁ ወይም ድንገተኛ እንደ መቅሰፍት፣ እድለኝነት፣ ህመም በሆኑ ምክንያቶች የሚያጋጥሙ የሕይወት ቀውሶችን ያጠቃልላል (ዝኒ ከማሁ፣ 205)። በጋብቻ ሽግግር የሚካሄድ ለውጥ በባህሪው በሰው ልጅ የሕይወት ዘመን የሚጠበቅ፣ ሁሉንም አካል፣ አእምሮና መንፈስ የሚቆጣጠር ሁነት ሲሆን የባለጉዳዩን የነበረና የረጋ ሁኔታ አፍርሶ ለአዳዲስ ሁኔታዎች የሚዳርግ፣ ለተለያዩ ግራ መጋባቶችና ጭንቀቶች የሚያጋልጥ፣ በመጨረሻም ወደ ሌላ አዲስ መዋቅር የሚያደርስ ሂደት እንደሆነ ይገለጻል (ዝኒከማሁ፣ 206-207)። ለውጡም ከባለጉዳዩ ሚና እና ደረጃ ባሻገር ማህበራዊና መንፈሳዊ ግንኙነቱ ላይም አሻራውን ያሳርፋል (ብራና-ሹቴ እና ግሬይ፣ 1979፡ 59) እና (ቤል፣ 1997፡ 94-95)።

## 1. የአጠናን ዘዴ

ይህ ጥናት በሰዎች አመለካከት፣ አስተሳሰብና ባህሪ ላይ የሚያተኩር፣ በትንተና፣ በትርጎማና በፍከራ ፍች የሚሰጥ በመሆኑ ዓይነታዊ ነው። በዚህ ጥናትም ከአጠቃላይ ተጠኝ ወረዳ ውስጥ ማህበረሰቡን ሊወክል የሚችሉ ቀበሌዎችና መረጃ ሰጪዎች በአላማ ተኮር የናሙና አመራረጥ ዘዴ ተመርጠዋል። መረጃዎች ከቀዳማይና ከካልአይ ምንጮች ተሰብስበዋል። ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ተሳትፏዊና ተሳትፏዊ ያልሆነ ምልከታ፣ ነጻ ቃለ መጠይቅና ተተኳሪ የቡድን ውይይት ዘዴዎች ናቸው። ይህም አጥኝው የባህሉ ባለቤት በመሆኑ አመች ሆኖ አግኝቶታል። ካልዓይ የመረጃ ምንጮች ደግሞ አብያተ-መጻህፍት፣ ድረ-ገጾች፣ መጣጥፎች ሲሆኑ ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጽንሰ ሀሳቦችና ንድፈ ሀሳቦች የተሰበሰቡበት ነው። የመረጃ ትንተናው የተካሄደው በይዘት ሲሆን አቀራረቡ ደግሞ በገለጻ፣ በትረካና በትርጎማ ስልት ነው።

## 2. በጋብቻ ሽግግር ወቅት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች

የጋብቻ ሽግግር በሰፊው ሲታይ ከዕጮኝነት ጀምሮ ሙሽሮች ተላምደው ጎጆ እስከሚወጡ ያለውን ሂደት ያጠቃልላል። ሆኖም የዚህ ጥናት ትኩረት ዋናው ሽግግርና ለውጥ የሚካሄድበት ከሰርግ ዋዜማ ጀምሮ እስከ ጫጉላ ግላጭ[15] ድረስ ባለው ጊዜ የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ናቸው። በመጀመሪያ ሙሽሪት በእናቷ ቤት እያለች የጋብቻው ሥርዓተ ክዋኔ ክፍል የሆኑት ዳስ[16] የመስራት፣ የሙሽሪትን ምሪ[17] የመፍታት፣

15 የሙሽሮች የጫጉላ ጊዜ የሚያበቃበት ሥነ ሥርዓት ነው።

16 ለእንግዳ ማረፊያ የሚሆን ጊዜያዊ አዳራሽ ሲሆን ሰርጉ እንዳበቃ ይፈርሳል።

ሙሽራውን የመፈተንና ቃል የማስገባት እንዲሁም የዙረሽ ግቢ[18] ሥርዓቶች ይፈጸማሉ። ቀጥሎም ሙሽሪት ወደ ሙሽራው ቤተሰብ ከሄደች በኋላ በሚኖራት የጫጉላ ቤት ቆይታ ደግሞ ሙሽሮችን የተለየ ምግብ መመገብ፣ ጥበቃና እንክብካቤ ማድረግ፣ የጫጉላ ቤት ጨዋታ፣ ሙሽራ አጫዋች መመደብ፣ ሙሽራ ጠያቂ መላክና የጫጉላ ግላጭ ሥርዓቶች ይፈጸማሉ። በሙሽሪትም ሆነ በሙሽራው ቤት የሚፈጸሙ ሥርዓት ከዋኔዎች በሴቷ ዙሪያ የሚያጠነጥኑ እና የእሷን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል የሚከናወኑ ሲሆኑ እነሱም እንደሚከተለው ቀርበዋል።

## 2.1. በዋዜማ የሚከናወኑ ሥርዓተ ከዋኔዎች

በጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ ዋናው ጋብቻ ከሚፈጸምበት አንድ ቀን ቀደም ብሎ (በዋዜማ) ከሚከናወኑ ሥርዓተ ከዋኔዎች መካከል ዳስ መስራት፣ ምሪ መፍታት፣ ዳውጃ መርገጥ፣ ሙሽራ መፈተንና ቃል ማስገባት እንዲሁም ዙረሽ ግቢ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

### 2.1.1.ዳስ መስራት

ዳስ በወንዱም ሆነ በሴቷ ቤት የሚከናወን ሲሆን ቅዳሜና እሁድ ለሚከናወን ሰርግ አርብ ዕለት የሚዘጋጅ ለእንግዳ ማረፊያ የሚያገለግል ዳስ እና ለስጋ መቁረጫ የሚውል ሽንበቆ (ቃዛ) ተፈልጎ ይመጣል። ቅዳሜ ጠዋት ሽማግሌዎች ተሰባስበው፣ የንስኃ አባት ጠርተው ፍሪዳው[19] ይጣላል። እዚያው ላይ ከትኩሱ ስጋ በቅቤ ኩርፍ ጥሬ ስጋ እየዘለዘሉ እየጠበሱ ወይም በጥሬው ይበላሉ። ለወጥ የሚሆንም ከላዩ ላይ ለሴቶች ይሰጣቸዋል። በደረሰ ጊዜ ሁሉም ይበላል፤ ይጠጣል። በመጨረሻ ተመርቆ ሁሉም ወደ ቤት ገብቶ አታሞ/ከበሮ እየተመታ ይጨፈራል። ይህም ሰርጉ በይፋ የተጀመረ መሆኑን የሚያበስር ነው። በዚህ ጊዜ ሁሉም ካለበት እየመጣ ሰርጉን ይቀላቀላል፤ ሆኖም የመጣውም ያልመጣውም "መጥታችሁ ልጃችሁን መርቁ!" እየተባለ አገርተኛው ህዝብ በሙሉ ይጠራል። ደስታውም የጋራ ይሆናል፡፡

### 2.1.2. ምሪ የመፍታት ሥነ ሥርዓት

በዋዜማ ከሚከናወኑ ሥነ ሥርዓቶች መካከል ሁለተኛው የሙሽሪትን ምሪ መፍታት ነው። ምሪውን የምትፈታው ቀጣይ ልትዳር የምትችል ልጃገረድ ጓደኛዋ፣ ታናሽ እህቷ/ዘመዷ ስትሆን በምትኩ መቀነት እንድትታጠቅ ይደረጋል። ምሪ የልጅነትና የድንግልና ምልክት ሲሆን በምትኩ የምትታጠቀው መቀነት ደግሞ ለአካለ መጠን መድረስን፣ ትልቅነትንና ሚስትነትን አመላካች ተደርጎ እንደሚወሰድ ይገለጻል። ምሪውን

17 ከከብት ቆዳ የተሰራ ልጃገረዶች በወገባቸው የሚታጠቁት መታጠቂያ ሲሆን ያንን የታጠቀች ሴት ልጅ ያላገባች መሆኗን አመላካች ነው።

18 ዙረሽ ግቢ፣ በሙሽሪት ቤት የሚፈጸም ሲሆን ወንድ ሙሽራና ሚዜዎቹ መጥተው ሲበሉ፣ ሲጠጡና ሲዘፍኑ አድረው ሊነጋ አካባቢ ሙሽሪትን ተረክበው ይዘዋት ወጥተው ትንሽ ከቆዩ በኋላ የሚመለሱበት ሥነ ሥርዓት ነው።

19 የተቀለበ የእርድ ከብት ወይም ሰንጋ

የፈታችላት ልጃገረድ ወዲያውኑ በወገቧ ታጥቃ ወይም በራሷ ላይ አስራ ትጨፍራለች። በወቅቱም እንዲህ እየተባለ ይዘፈናል።

ታጠቂው በቡጥጫ-----አይገኝምና የእናት ዋንጫ
ታጠቂው በጎመሮ-----ከያዘ አይለቅም አባ ነብሮ
ታጠቂው በዠንገደር-----አይገኝምና ከአባት ማደር/ አይገኝምና ከእናት ማደር
ታጠቂው በሳር ለምለም-----አይገኝምና ወለም ዘለም
ታጠቂው በጠቀርሻ-----አይገኝምና የአባት ጉርሻ እየተባለ ይዘፈናል (ወ/ሮ አስረሴ፣ 23/08/2013 ዓ.ም የተካሄደ ቃለ መጠይቅ)።

ከላይ የቀረበው በዘፈን የሚከወነው ቃል ግጥም ሙሽሪት ምሪዋን ስትፈታ አብራ የምታጣቸው፣ የሚጠብቋትና የምትጀምራቸው አዳዲስ ግላዊና ማህበራዊ ሚናዎች መኖራቸውን ያሳያል። ልጅነት እና ከልጅነት ጋር የተያያዙ ከእናት ከአባት ጋር ማደር፣ በእጃቸው መጉረስ፣ በዋንጫቸው መጠጣት፣ ከእነሱ መዋል ማደር ወይም መኖርና የመሳሰሉ የለመደቻቸው ነገሮች ከፈታችው ምሪ ጋር ላይመለሱ የሚቀሩ ናቸው። በምትኩ ከምትታጠቀው መቀነት ጋር የሚጀመሩ፣ ከማያውቁት ሰው ጋር መዋል ማደርና መኖር፣ እንዲሁም ጋብቻን ተከትለው የሚጀመሩ ጾታዊ ግንኙነቶች፣ ራስን መቻል የመሳሰሉ ጉዳዮች እንደሚጠብቋት ይገልጻል።

ምሪ የመፍታት ሥነ ሥርዓት የሙሽሪት የልጅነት ጊዜ ማብቃቱን፣ ለዘር ፍሬ የሚበቁበት ግንኙነት የሚጀመርበት መሆኑን የሚያውጅ ነው። ይህንንም ቀጥሎ በሚከናወነው ሙሽሪትን ለሙሽራው የማስረከብ ሥነ ሥርዓት ላይ ሽማግሌዎች ጋብቻውን የእውነት ያርገው፣ ህጋቸውን ይባርክልን፣ ይልመዱ፣ ይክበዱ፣ ይውለዱ፣ ለፍሬ ያብቃቸው እያሉ በሚመርቁት ምርቃት ፈቃዳቸውን ይሰጣሉ (ምልከታ፣ 25/05/2012 ዓ.ም የተካሄደ)። ይህም ሙሽሪት የሚጠብቋትን ግላዊና ማህበራዊ ሚናዎች ምን ምን እንደሆኑ የምታውቅበትና ለዚያም ዝግጅት እንድታደርግ ፍንጭ የምታገኝበት ሁነት ነው።

### 2.1.3. ዳውጃ የመርገጥ ሥነ ሥርዓት

ዳውጃ መርገጥ ወንድም ሆነ ሴት ሙሽራ የሚከውኑት ነው። ሆኖም በምልከታ ማረጋገጥ የተቻለው የሴት ሙሽራን በመሆኑ እሱን ማሳየቱ ተመራጭ ሆኗል።
በሰርግ ዋዜማ ሙሽሪት በተገዛላት አልባሳት እና ጌጣጌጦች አምራና ተውባ እኩለ ሌሊት አካባቢ ሲሆን ከተደበቀችበት ማጀት[20] ተውባ፣ ተሸፋፍና እና ታዝላ፣ እልል እየተባለ፣ በጨለማው ጥላዋን ዘርግታ ተሸፋፍና ወደ ሳሎን ወይም ወደ ዳስ እንድትመጣ ይደረጋል። እንደመጣችም ከወለሉ መሀል ላይ በጀንዲ[21] ላይ ሲያስቀምጧት ሰርገኛ/ቤተ

20 ዕቃ ቤት

21 ከከብት ቆዳ የተሰራ ለመኝታ የሚያገለግል ምንጣፍ

ዘመድ ሙሽሪትን ዙሪያዋን በመክበብ ይጨፍራል። ወላጆች፣ ታዳሚ ሽማግሌዎች፣ መነኩሴዎች ትዳራቸው እንዲቀና፣ ሀብታቸው እንዲባረክ መመኘትና የሚጠብቃቸውን ግላዊና ማህበራዊ ሃላፊነት የሚገልጹ ምርቃቶችን ይመረቃሉ። ምርቃቱን የምትጀምረው ወላጅ እናት ስትሆን አባት ይቀጥልና ሽምግሌዎች ከዚያም መነኩሴ መርቆ በቄስ ጸሎት ሲጠናቀቅ ዳውጃ ረገጡ ይባላል፤ ጋብቻውም እንደተፈጸመ ይቆጠራል (07/06/2012 ዓ.ም፣ ዱምሪ ኪዳነ ምህረት የተካሄደ ምልከታ)። ከዚህ በኋላም ሙሽሪት ለሙሽራው በክብር ትሰጠዋለች። ሙሽሮች ከሚመረቋቸው ምርቃቶች መካከል ተከታዩን እንደ ምሳሌ ማንሳት ይቻላል።

> ጋብቻውን የእውነት ያርገው፣ ህጋቸውን ይባርክልን፣ ይልመዱ፣ ይክበዱ፣ ይውለዱ፣ ሀብታም ከብታም ያድርግልን፣ የተቆረጠላቸውን ሀብት ያቅናው፣ የአያታቸው የቅማታቸው ሀብት በነሱ ላይ ይደር፣ ወልደው ከብደው እንዲኖሩ ያድርግልን፣ ከእናት አባታቸው ፈቃድ አያውጣቸው፣ ቤተ ክርስቲያን እሚሰሩ ሃይማታቸውን እሚጠብቁ ያድርጋቸው፣ ተምረው፣ አድገው፣ ቦታ እሚያስከብሩ፣ ዘመድ እሚጠቅሙ ያድርጋቸው፣ ደም መላሽ ያርጋችሁ፣ እንደ መንግስት መንግስት ያርጋችሁ፣ እንደ ካህን ካህን ያርጋችሁ (07/06/2012 ዓ.ም፣ ዱምሪ ኪዳነ ምህረት የተካሄደ ምልከታ)።

በዚህም ሙሽሮች ከጋብቻ በኋላ የሚጠብቋቸው፣ እንዲያከናውኗቸው የሚፈልጓቸው፣ እንዲሆኑ የሚመኙላቸው ተግባርና ምግባር በግልጽ ይታወቃል።

### 2.1.4. ሙሽራ መፈተንና ቃል እንዲገቡ ማድረግ

ሙሽራ መፈተንና ቃል እንዲገቡ ማድረግ በዋዜማው ሌሊት ላይ ሙሽሪት ወላጆች ቤት የሚፈጸም ሲሆን ሙሽራው ከነሚዜዎቹ ገብቶ ከተጋበዘ በኋላ የሙሽራው ተወካይ የሆኑት ሶስት ሚዜዎቹ በሽማግሌ እና በሙሽሪት ዘመድ አዝማድ ፊት ቀርበው ከሙሽራው ጋር ስላላቸው ዝምድና ከተጠየቁ በኋላ ሙሽሪት በጫጉላ ቤት ስትቆይ ደህንነቷ የተጠበቀ እንዲሆን ቃል ይገባሉ (07/06/2012 ዓ.ም መንደር ኪዳነ ምህረት ቀበሌ የተካሄደ ምልከታ)። በዚህ መሰረት ሚዜውም ሙሽሪትን ለሙሽራው እናት (ለአማቷ) ከልጃቸው እንደማይለዩኣት ቃል አስገብቶ ያስረክባል። አንደኛ ሚዜ (ስር ሚዜ)፣ ሁለተኛ ሚዜና ሶስተኛ ሚዜዎች ከሽምግሌዎች ፊት ለፊት ቀርበው ተራ በተራ አስተውሎታቸውና እውቀታቸውን የሚመለከቱ ጥያቄዎችን ይጠየቃሉ። ሙሽሪት በእንግድነት ስትቆይ ደህንነቷ የተጠበቀ እንዲሆን ቃል እንዲገቡ ይደረጋል፡፡ የጥያቄዎች ዋና ጭብጥ ከሙሽራው ጋር ስላላቸው ዝምድና፣ በቆይታዋ ስለሚያደርጉላት እንክብካቤ የንስኃ አባታቸውን ስም እየጠሩ ይምላሉ፤ ይገዘታሉ፤ ቃል ይገባሉ (07/06/2012 ዓ.ም፣ ዱምሪ ኪዳነምህረት የተካሄደ ምልከታ)።

ምንም እንኳን ሶስቱም ሚዜዎች ቃል ቢገቡም አንደኛ (ስር) ሚዜ ግን ከሁለቱም በበለጠ ሙሽሪት በአማቶቿ ቤት በዋናነትም በጫጉላ ቤት ስትቆይ እንግድነትና ብቸኝነት እንዳይሰማት ሁኔታዎችን በማመቻቸት በኩል ጉልህ ሚና ይጫወታል። ይህ ሙሽራ

የመፈተንና ቃል የማስገባት ሥነ ሥርዓት በሙሽሪት ቤተሰብና ዘመድ ፊት የሚካሄድ በመሆኑ ሙሽሪት ደህንነትና መረጋጋት ይሰማታል። በተለይ በሙሽራውና በሚዜዎች መካከል ያለውን ዝምድና ሲሰሙ፣ በጫጉላ ቤት ቆይታቸው ከአጠገባቸው እንደማይለዩ በንስኃ አባታቸው ሲገዘቱ እምነት ያድርባቸዋል። ሙሽራን መፈተንና ቃል ማስገባት ለሙሽሪት ደህንነት እንደ ዋስትና የሚታይ በመሆኑ ሌላው የለውጥ ማለማመጃ ብልሃት ተደርጎ ይወሰዳል።

### 2.1.5. የዙረሽ ግቢ ሥነ ሥርዓት

በሰርግ ዋዜማ ከሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች የመጨረሻው የዙረሽ ግቢ ሥነ ሥርዓት ነው። የሚከናወነውም የወንድ ሙሽራና ሚዜዎቹ ወደ ሴት ሙሽራ ቤት ከገቡ በኋላ እስከ ንጋት ድረስ እየበሉ፣ እየጠጡና እየዘፈኑ አምሽተው በመጨረሻ ሙሽሪትን ተረክበው ወጥተው ከትንሽ ቆይታ በኋላ ተመልሰው የሚገቡበት ነው። ሲገቡም ሙሽሮች በጋራ እጅ ለእጅ ተያይዘው በግ እንዲያርዱና እንዲራመዱት ይደረጋል። ሚዜዎችም ሞቅ ያለ ዘፈን ዘፍነው በልዩ ሁኔታ የተዘጋጀላቸውን በቅቤ ኩርፍ እንጀራና ወፍራም ጠላ በመሻማት በልተውና ጠጥተው ይወጣሉ። ከዚያም ሙሽሪትን ለቤተሰቦቿ አስረክበው ቀኑን ሙሉ ሲበሉ፣ ሲጠጡና ሲዘፍኑ ይውላሉ። በመጨረሻም በዋናው የሰርግ ዕለት ወደ እኩለ ሌሊት ገዳማ ለመጨረሻ ጊዜ ይዘዋት ይሄዳሉ። ሲሄዱም በተለያዩ ቡድኖች ሞቅ ያለ ክዋኔ ይከወናል። በሴቶች ቡድን ከሚከወኑ ቃል ግጥሞች መካከል የሚከተሉትን እንደ ምሳሌ መጥቀስ ይቻላል።

ሙሽራየ ሆይ፣
እንዳንች አያምሩም ወይ፡፡
ተውበሻል እቴ፣
የብር መስታይቴ፡፡
አጀባ ነው ሰውሽ፣
በየት ልይሽ፡፡
እንዳላይሽ፣
ዳመናው ጣለ በላይሽ፡፡
እንዳልነካሽ፣
በወርቅ ሚዛን ተለካሽ፡፡

እየተባለ ይዘፈናል (ዱምሪ ኪዳነ ምህረት ቀበሌ፣ 08/06/2012 ዓም የተካሄደ ምልከታ)።

የዙረሽ ግቢ ሥነ ሥርዓት ሙሽሪት ከቤተሰብ መለየትን የምትለማመድበትና ጫናውንም መቋቋም እንድትችል ቅድመ ዝግጅት እንድታደርግ ያግዛታል።

### 2.2. በጫጉላ ቤት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች

በዚህ ክፍል ሙሽሪት ወደ ወንድ ሙሽራ ከሄደች በኋላ በጫጉላ ቤት የሚከናወኑ ጉዳዮች ቀርበዋል። እነሱም ለሙሽሮች የተለየ ምግብ መመገብ፣ ሙሽራ አጫዋች መመደብ፣ የጫጉላ ቤት ጨዋታ፣ ሙሽራ ጠያቂ መላከና የጫጉላ ግላጭ ዋና ዋናዎቹ ሲሆኑ በተናጠል ምን እንደሚመስሉ ቀጥሎ ቀርበዋል።

### 2.2.1. ሙሽሮችን የተለየ ምግብ መመገብ

በጃቢ ጠህናን ማህበረሰብ ዘንድ ሙሽሮች በጫጉላ ቤት ሲቆዩ የተለየና የተመረጠ ምግብ እንዲመገቡ ይደረጋል። እስከ ጫጉላ ግላጭ ድረስ እንደየሰው እና እንደየቤቱ ሁኔታ ሙሽሮች ጭብጦ[22]፣ ዶሮ፣ ስጋ፣ ወተት፣ እንቁላል እየተመገቡ ይቆያሉ። በዚህ መንገድ ያለፉ ሴት መረጃ ሰጭዎች በጫጉላ ቆይታቸው አንዳንዶች ጭብጦ[23] ሌሎች ደግሞ ሙሉ ዶሮ እንዲሁም ስጋ፣ እንቁላልና ወተት እየተመገቡ እንደቆዩ አስረድተዋል። ይህም ጋብቻ ሙሽሪት ድንግልናዋን የምታጣበት አጋጣሚ በመሆኑ፣ ሰውነትን ለመጠገን፣ ድካምን ለመቀነስ፣ አቅምን ለማጎልበት ባጠቃላይ ያጣችውን ኃይል ለመተካት ሲባል እነዚህን ምግቦች መመገብ እንደሚገባት ይነገራል። ይህ በአማቷ ቤት የሚደረግላት እንክብካቤ ጋብቻውን እንድትወደውና እንድትለምደው የሚያግዝ በመሆኑ ይህም እንደ ለውጥ መለማመጃ ይቆጠራል።

### 2.2.2. ሙሽራ አጫዋች መመደብ

ሙሽራ አጫዋች በጫጉላ ቤት ቆይታ ሙሽሪትን የምትጠብቅ፣ በቅርብ የምትከታተል፣ የምታጊያጊጥ፣ የምትንከባከብ፣ ከሰውም ሆነ ከአካባቢው ጋር የምታላምድ የቅርብ ጓደኛ ናት። ሙሽራ አጫዋች ሙሽሪትን በጠዋት ወደ መጸዳጃ ቦታ ከመውሰድ ጀምሮ መሸቶ እስከትተኛ ድረስ አብራት ትሆናለች። ሙሽሪትን የምታጊያጊጣት፣ ምግብ የምታባላት፣ ስጦታ የምትቀበልላት፣ ሚስጥሯን የምታጋራት፣ የአዳር ገጠመኟን የምታወራት ጓደኛዋ ናት። የተመደበችው አጫዋች ያገባች ከሆነች በህይወት ልምድ የታገዘ ሙሽሪት ከባሏ ጋር ስለሚኖራት ግንኙነት፣ ስለ ጾታዊ ግንኙነቶች ጭምር ምክር ትሰጣታለች። የተለያዩ ሴቶች ያጋጠማቸውን ሁኔታ ባጋሩበት ተተኳሪ የቡድን ውይይት ላይ እንደገለጹት የአንዳንዶች አጫዋች ሁሉንም ነገር በድፍረት እንዲፈጽሙት የሚያበረታቱ ሲሆኑ የአንዳንዶች ደግሞ ማምለጥ የሚችሉባቸውን ብልሃቶች ልምዳቸውን አስደግፈው የሚጠቁሙ እንደነበሩ አስረድተዋል (23/05/2012 ዓ.ም በተካሄደ የተተኳሪ ቡድን ውይይት)። ባጠቃላይ ሙሽራ አጫዋቾች ሙሽሪትን ከመንከባከብና ከማጊያጊያጥ ባሻገር በህይወት ልምድ የዳበረ ምክር በመምከር ለሚጠበቀው ለውጥ የሚያዘጋጁ፣

22 ከጤፍ ዱቄት ተዘጋጅቶ የሚጋገርና በትኩሱ በቅቤና በበርበሬ ታሽቶ እየተጨበጠ የሚበላ የምግብ ዓይነት

23 ከአፍለኛ ጤፍ ዱቄት የተጋገረ ቂጣ በቅቤና በበርበሬ ታሽቶ የሚሰራ የምግብ አይነት ሲሆን በብዛት የአራስ ምግብ ነው። በምጥ የተጎዳን ወገብ ይጠግናል ተብሎ ይታሰባል።

የሚያበረታቱና ለውጡ ከደረሰ በኋላም የማጽናናት ተግባር ስላላቸው፣ ሄደቱ እንደ ጋብቻ ለውጥ ማለማመጃ ዘዴ ይወሰዳል።

### 2.2.3. የጫጉላ ቤት ጨዋታ (የደገም)

የጫጉላ ቤት ጨዋታ (የደገም) የተገኘው ሁሉ የሚሳተፍበት፣ ሙሽሮችን እርስበርስ የሚያላምድና የሚያቀራርብ መሆኑ ይገለጻል። አጨዋወቱ ከሙሽሪት ጀምሮ ተራ በተራ አይናቸውን እየሸፈኑ ጭንቅላታቸውን በእጅ መምታትና የመታቸውን መለየት ነው፤ የመታውን እስከሚያውቅ ድረስ በተደጋጋሚ ይመታል (አቶ ዘለቀ፣ 23/05/2012 ዓ.ም የተካሄደ ቃለ መጠይቅ)። ይህ ጨዋታ ሁሉን አሳታፊ ስለሆነ ሙሽሪት በቀላሉ እንድትላመድና እንድትግባባ ይረዳታል። በሌላ በኩል ሙሽሪትን በእንግድነቷ ምክንያት በጣም እየመቱ እንዳያሳምሟትና እንዳያስከፏት ሙሽራው (ባል) በተቆርቋሪነት ስሜት ይጠብቃታል። ይህም ሙሽሪት ሙሽራውን እንድትቀርበው መንገድ ይከፍታል። የደገም የሙሽሮችን የጫጉላ ቤት ቆይታ አስደሳችና የማይረሳ ያደርገዋል ይላሉ። በተለይ የሙሽሪትን የእንግድነት ስሜት በመቀነስ በቶሎ እንድትላመድ የሚረዳ በመሆኑ የጋብቻ ለውጡን የመለማመጃ አንድ ብልሃት ይታያል።

### 2.2.4. ሙሽራ ጠያቂ መላክ

ሙሽሪት ካደገችበት ቤት ወጥታ፣ ከቤተሰቦቿ ተለይታ በአማቶቿ ቤት ስትቆይ የሚሰማትን የብቸኝነት ስሜት ለመቀነስና በቤተሰቦቿ ናፍቆት እንዳትጎዳ ለማድረግ በሄደች በሁለተኛው ወይም በሶስተኛው ቀን ታላቅ እህት/ አክስት/ ወንድም/ አጎት እንጀራና ጠላ፣ ዳቦ፣ ሎሚ፣ ሸንኮራ አገዳ በመያዝ ሄደው ልጃቸው በምን ሁኔታ ላይ እንዳለች የማየትና የመጠየቅ ልማድ ነው። ይህም ለሙሽሪት ደስታና መረጋጋት ከመስጠት ባሻገር ቤተሰብ እንዳላት እንድታስብና ተስፋ እንዳትቆርጥ ያስችላታል። በዚህ አጋጣሚ ቤተሰቦቿ የልጃቸውን መመቸት እና አለመመቸት ይረዳሉ። የሙሽሪትን ፊት አይተው እንዳልተመቻት ካሰቡ አንደኛ ሚዜውን ጠርተው “ልጃችን ምን ሆና ነው? በአንድ ቀን እንዲህ የሆነችው? በቤታችሁ ባገራችሁ እህል የለም?” በማለት የልጃቸውን አለመመቸት ይነግራሉ። አያያዛቸውን እንዲያስተካክሉም ማስጠንቀቂያ የሚሰጡበት በመሆኑ ሙሽሪት ትረጋጋለች፤ ትደሰታለችም።

### 2.2.5. የጫጉላ ግላጭ

የጫጉላ ግላጭ የሰርጉ አካልና የመጨረሻው ሁነት ሲሆን ሙሽሮች ዋናውን የሙሽርነት ጊዜ ጨርሰው ወደ ማህበረሰቡ የሚቀላቀሉበት ሥነ ሥርዓት ነው። በተለይ ሙሽሪት በጫጉላ ቤት ስትቆይ ከብዙ ነገሮች ተገድባ፣ በነጠላዋ ተሸፍና የምትቆይ በመሆኑ በዕለቱ ከነጠላዋ የምትገለጥበትና የጫጉላ ጊዜ አብቅቶ የምትወጣበት ሁነት በመሆኑ ሞቅ ደመቅ ባለ ሁኔታ ይከበራል። ቀደም ባለው ጊዜ ሙሽሮች ጫጉላ ቤት የሚቆዩት ለአርባ ቀናት ያህል እንደነበረ ይነገራል። አሁን አሁን እንደሁኔታው ለአስር እና ለአምስት ቀናት ይቆያሉ (አቶ ታምሩ፣ 25/05/2012 ዓ.ም የተካሄደ ቃለ መጠይቅ)። በመሆኑም

የሙሽሪት መልክና ቁመና የሚታየው በዚሁ ዕለት ነው። በቆይታቸው ለአማቶቻቸው ፍታይ አልብሰው ለቤታቸው ስፌት አሟልተው ይገለጡ እንደነበር ይነገራል። በግላጩ ዕለትም ሙሽሪት እንደተገለጠችም የሰፋችው ስፌትና የፈተለችው ፈትል እየታየ ትመረቅ ነበር ይላሉ (አቶ ለገሰ፣ 23/05/2012 ዓ.ም የተካሄደ ቃለ መጠይቅ)። የግላጩ ሥነ ሥርዓት ከተከናወነ በኋላ ወደ ሙሽሪት ቤት ሲደርሱ ቤተሰብና ዘመድ አዝማድ ተሰብስበው እንዲህ በማለት እየዘፈኑ ይቀበሏቸዋል።

እንኳ መጣሽ እቴ የብር መስታይቴ፣
እንኳ መጣህ አያ ያ'ባይ ዳር ሱማያ።

እያሉ ይቀበሏቸዋል። ከዚያም ያመጡትን የእጅ መንሻ በግ አርደው ወደ ውስጥ ይገባሉ። ለመስተንግዶ የተመረጡ የሙሽራው ዋና ዋና ሚዜዎች የታረደውን በግ ሰርተው ያበላሉ። ግላጭ የጋብቻው ውጤት የሚታይበት በመሆኑ ሽግግሩ በሰላም ከተካሄደና የታሰበው ለውጥ ከተገኘ (የሙሽሪት ድንግልና ከተገኘ፣ መልክ ከምግባር ያሟላች ከሆነች፣ ባለሙያ ከሆነች) እራሷ ሙሽሪትና ወላጆቿ የሚወደሱበትና የሚመሰገኑበት ነው።

ከተበላና ከተጠጣ በኋላ የሙሽሪት ወላጆች በዋናነት ሙሽሪት ከነ ክብሯ በመገኘቷ፣ ቀጥሎም ቆንጆ የወለዱና በጥሩ ምግባር ያሰደጉ በመሆናቸው፣ ባለሙያ በመሆኗ እንዲህ እየተባሉ ይመሰገናሉ።

የሙሽሪት አባት ከላይ ይቀመጡ፣
የሙሽሪት እናት ከላይ ይቀመጡ፣
አሳድገዋታል እየቆነጠጡ።
ሙሽሪት ለምዳለች፣
ከእናቷ ከአባቷ ባሏን ትወዳለች።
ሙሽሪት ለምዳለች፣
እንዝርቴን ደጋኔን ላኩልኝ ብላለች።

ሙሽሪትም ምንም እንኳ የመጣችው ወደ ኖረችበት ቤትና ወዳሳደጓት ቤተሰቦቿ ቢሆም ከባሏ ጋር ወደ ውስጥ ትገባለች። ከዚያም የሙሽሪት እህት ወይም አክስት "ልጃችንን ላኩልን ሰላም እንበላት" በማለት የሙሽራውን ወይም የሚዜውን ፈቃድ ከጠየቁ በኋላ ለሰላምታ ቤተሰቡን ትቀላቀላለች (25/05/2012 ዓ.ም፣ ምርጫ ቀበሌ የተካሄደ ምልከታ)። ይህም ከጋብቻ በኋላ ሙሽሪት ወልደው ካሳደጓት ቤተሰቦቿ ይልቅ ከባሏ መቅረቧን ያመለክታል።

የጋብቻ ሽግግር አስገዳጅ ቢሆንም ለውጡ አዎንታዊ ትርጉም ስላለው ሙሽሮች በቶሎ እንዲቀበሉት ይፈለጋል። በተለይ ከጫጉላ ግላጭ በኋላ በሰርግ ዋዜማ እና ጫጉላ ቤት ይደረጉ የነበሩ እንክብካቤዎች ቀርተው ጫናው በተጋቢዎች ላይ ብቻ የሚቀጥል በመሆኑ ከባድ ይሆናል። ሆኖም ሙሽሮች ከትዳር አጋራቸው ጋር ተላምደው፣ ቤት

ሰርተው ከብደው ወልደው ራሳቸውን ችለው መኖር እስከሚጀምሩ ድረስ የወላጆቻቸው ክትትል አይለያቸውም። ለሙሽሮች የትዳርን፣ ራስ የመቻልን፣ የመልመድን፣ ቤት የመስራትን መልካምነት ከመምከር ባለፈ በተለያዩ ዘዴዎች እንደሁኔታው ተግባራዊ ይደረጋሉ።

## 3. የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎች ሚና

በጃቢ ጠህናን ወረዳ ማህበረሰብ ዘንድ በጋብቻ ሽግግር ወቅት የሚፈጸሙ ስርዓተ ክዋኔዎች ለሙሽሮችና ለቤተሰቦቻቸው እንዲሁም ለአጠቃላይ ማህበረሰቡ የሚያበረክቷቸው የተለያዩ አላማና ሚና አላቸው። እነሱም እንደሚከተለው ቀርበዋል።

### 3.1. የቅድመ ጋብቻ ዝግጅት ማድረጊያ

በጃቢ ጠህናን ወረዳ ባህላዊ ጋብቻ የሚፈጸመው ከሙሽሮች እውቅናና እና ፈቃድ ውጭ፣ በልጅነት እድሜ በመሆኑ፣ በጥንዶች መካከል የቀደመ ትውውቅ ባለመኖሩና ሁሉም ነገር የሚያልቀው በወላጆች ፍላጎትና እቅድ መሰረት በመሆኑ በተለይ ሴቶች ለበለጠ ጭንቀትና ግራ መጋባት ይዳረጋሉ። ሆኖም በጋብቻ ሽግግሩ ወቅት በሚፈጸሙ ሥርዓቶች፣ ቃል ግጥሞችና ምርቃቶች አማካኝነት ልታገባ እንደሆነ፣ ልጅነቷ እንዳበቃ፣ ጾታዊ ጉዳዮች የሚጀመሩበት እንደሆነ፣ ልዩ ልዩ ግላዊና ማህበራዊ ሚናዎች እንደሚጠብቋት ይነገራታል። ምሪ የመፍታት ሥነ ሥርዓቱ እሷን ማዕከል ያደረገ ሲሆን፣ በወቅቱ በሚከወኑ ሥርዓቶችና ቃል ግጥሞች ልጅነቷ ማብቃቱ ይጠቆማል፤ በምርቃት ተጋቢዎች ጋብቻውን እንዲለምዱ፣ እንዲከብዱ፣ እንዲወልዱ ሲነገራቸው ከጋብቻው በኋላ የሚጠብቃቸውን ተግባርና የሚያስከትላቸው ውጤቶች ዙሪያ እውቅና በመስጠት ራሷን እንድታዘጋጅ የማድረግ ሚናቸውን ይወጣሉ።

### 3.2. ሽግግሩን ማጀብ

የጋብቻ ሽግግር በባህሪው ጠበቅ ያለ ባለጉዳይን በኃይል አፍርሶ እንደገና የሚሰራ፣ ወደቀጣዩ የሕይወት ምዕራፍ የሚያሻግር፣ በሚገባ ካልተያዘ ለከፋ አደጋ የሚያጋልጥ ወሳኝ ሁነት በመሆኑ የሽግግር ወቅቱ በልዩ ልዩ ሥርዓተ ክዋኔዎች ይታጀባል። የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔ ዋናው ግብ ሙሽሮችን ወደ አንድነት ወይም አብሮነት ማሸጋገር እና የጥንዶችን የመጀመሪያ የግብረ ስጋ ግንኙነት ማክበር፣ ከጾታዊ ባህሪያትና ደንቦች ጋር የተያያዙ የአመለካከት ለውጦችን ማምጣትና ግለሰቡን በጾታዊ ባህሪው ላይ ለውጥ እንዲያካሂድ መርዳት መሆኑ ይገለጻል። በሽግግሩ የሚገለጡ ዋና ዋና የለውጥ ሂደቶችም የተለያየ ቅርጽ ባላቸው ባህላዊ አውዶች በሚከወኑ ሥርዓቶች ይገለጻሉ።

የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎች በሽግግር ወቅቱ የሚፈጠሩ ጥርጣሬዎችና ግራ መጋባቶች እንዲቀንሱና ሙሽሮች በትዳራቸው እርግጠኛ እንዲሆኑ፣ ጋብቻውን እንዲቀበሉት፣ እንዲያምኑበትና እንዲኖሩበት ያግዛሉ። ሙሽሮች በሥርዓተ ክዋኔው አማካኝነት የሚያደርጉት የሚና ሽግግር የማህበረሰቡን ደንብ ከማረጋገጥም ባሻገር እውቅና ለሚሰጠው ማህበረሰብም እንደ ማበረታቻ ነው።

### 3.3. ጥበቃ ለማድረግ
በሰርግ ዋዜማ ጀምሮ በጫጉላ ቤት የሚከናወኑ ሥርዓተ ክዋኔዎች ዋና ሚና ለሙሽሮች ጥበቃ ለማድረግ ሲባል የሚካሄዱ ናቸው። በተለይ ቃል ማስገባት ሙሽሪት በአማቶቿ ቤት በደህና እንድትቆይ የሚያደርጉ ናቸው። በመሆኑም በጫጉላ ቤት ቆይታቸው የሚደረጉ እንክብካቤዎች ዋና አላማ የሽግግር ወቅቱን አሳሳቢነት ለመቀነስ፣ ለውጡንም አዎንታዊ ለማድረግ ሲባል እንደሆነ ይገለጻል። የሰርግ ሥነ ሥርዓት ሙሽሮች ለመጀመሪያ ጊዜ የግብረ ስጋ ግንኙነት የሚፈጽሙበት በመሆኑ በብዙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ይታጀባል። ስለዚህ በጋብቻ ወቅት የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ዋና ዓላማ የሽግግር ወቅቱ በሰላም እንዲጠናቀቅና የሚጠበቀው ወይም የሚፈለገው የተጋቢዎች ለውጥ እንዲመጣ ባጠቃላይ የጋብቻ ሽግግሩ ግቡን እንዲመታ የሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው።

### 3.4. ህክምና የመስጠት (የመፈወስ) ሚና
የሽግግር ወቅት ባለጉዳይን ከነበረውም ሆነ ወደፊት ከሚሆነው ማንነት ውጭ ስለሚያደርግ ወቅቱ ጭንቀትና ግራ መጋባት የሞላበት መሆኑ ተገልጿል። በወቅቱ የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ባለጉዳዩንም ሆነ በዙሪያው ያለውን ማህበረሰብ ከጭንቀትና ከግራ መጋባት ያክማሉ። ጭንቀትን በመቀነስ፣ ሽግግሩ የግድ እንደሆነ እና እንዲያምኑት በማድረግ፣ ሽግግሩ ጤናማ እንዲሆን በማድረግ ረገድ ጉልህ ሚና ይጫወታሉ።

በጋብቻ ሽግግር ወቅት የሚፈጸሙ ክዋኔዎች የማከምና የመፈወስ ሚና እንዳላቸው ይነገራል። አስጊ እና አሳሳቢ የሆነው የሙሽርነት ጊዜ በሰላም አልፎ የታሰበው ውጤት መጥቶ ስነ ልቡናዊ እረፍት እንዲገኝ ከላይ የቀረቡት ክዋኔዎች ይፈጸማሉ። በዋናነት በሾተላይ ምክንያት በልጅ ሞት የተፈተኑ ሰዎች ልጃቸውን በልጅነት ይድራሉ። በምክንያትነት የሚገልጹት ልጆች ዳውጃ ሲረግጡ፣ ምሪ ሲፈቱ፣ በቤቱ ሲዘፈን ደስታ ሲሆን ባካባቢውም ያለ ርኩስ መንፈስ ይወገዳል የሚል ነው። ይህም ሰዎች በአንዳንድ የህይወት አጋጣሚዎች ሥርዓተ ክዋኔዎችን ካልፈጸሙ ጥሩ ያልሆነ ወይም ጎጅ ነገር እንደሚደርስባቸው ስለሚያስቡ ይህንን የፍርሃትና የጭንቀት ስሜት አስወግደው መረጋጋት እንዲሰፍን ያግዛል።

### 3.5. ባለጉዳይን ከሽግግሩ ጋር ማስማማትና ማለማመድ
ሽግግር ሁለት ተከታታይ የሆኑ የማይተዋወቁ ሁኔታዎችና ማንነቶች ለመገናኘት፣ አሮጌውን ትቶ፣ አዲሱን ይዞ ለመቀጠል የሚያስችል ሂደት በመሆኑ በወቅቱ የሚፈጸሙ ክዋኔዎች ተጋቢዎችን ለለውጥ የማዘጋጀት፣ ከአዲሱ ደረጃ ጋር የማገናኘት፣ የማይተዋወቁ ማንነቶችንና አካሎችን በማለስለስና በማስማማት የሚፈለገው ለውጥ እንዲካሄድ ትልቁን ድርሻ ይወጣሉ። ሥርዓተ ክዋኔዎችም ለውጡን ተላምደው እንዲቀጥሉ የማድረግ ሚና አላቸው። ተጋቢዎች ለሽግግሩ ራሳቸውን እንዲያዘጋጁ፣

ሽግግሩን በድፍረት እንዲያካሂዱና በሽግግሩ የተገኘውን ለውጥ መቀበል እንዲችሉ ይረዳቸዋል።

የጋብቻ ሽግግር የተጋቢዎችን ግላዊና ማህበራዊ ደረጃ ከመለወጥ ባሻገር ጾታዊና ማህበራዊ ግንኙነቶች የሚጀመሩበት በመሆኑ ውስብስብነቱ ከፍ ይላል። ሆኖም በወቅቱ የሚከወኑ ሥርዓተ ክዋኔዎች ይህን ውስብስብነትና ጭንቀት የመቀነስ ሚና ይኖራቸዋል። ከሙሽሮች የሚጠበቁ ሀላፊነቶችና ሚናዎች በማስተዋወቅና በማላመድ በአጭር ጊዜ ጋብቻውን እንዲቀበሉ ያግዛሉ፤ የደህንነት ማስጠንቀቂያ ይሰጣሉ። ሆኖም ይህ ጥበቃና እንክብካቤ ከግላጭ በኋላ የሚቀጥሉ ባለመሆናቸው፣ ሙሽሪት ሰርጉ ያስከተለውን ለውጥ ተቋቁማ እንድትቀጥል ይጠበቅባታል።

### 3.6. የባለጉዳይን ማህበራዊ ደረጃ ማሳወቅ (ለውጡን ማወጅ/ማረጋገጥ)

የጋብቻ ሥርዓተ ክዋኔዎች አንዱ ተግባር የባለጉዳይን ቀጣይ ሚና ማሳወቅ ወይም ለውጡን ማወጅ ነው። ለምሳሌ የጫጉላ ቤት ቆይታና የጫጉላ ግላጭ ሙሽሮች ከጋብቻው የሚጠበቀውን ሽግግርና ለውጥ ማካሄዳቸውን ማወጃ ወይም ማረጋገጫ ተደርገው ይታያሉ። ምክንያቱም የሙሽሮች ልጅነት አብቅቶ ትልቅነት፣ ከጋብቻ በፊት የነበረ ነጻነት አብቅቶ ለማህበራዊ ህግና ደንብ መገዛት የሚጀምሩበት በመሆኑ ነው። ለውጡም በአለባበሳቸውና በአጊያጊያጣቸው፣ በንግግራቸው፣ በአረማመዳቸውና በአጠቃላይ እንቅስቃሴያቸው፣ እንዲሁም በአመጋገባቸው ላይ ጭምር በግልጽ ይታያል። በሌላ በኩል ሙሽሪት አገልግሏ ውስጥ ከሚደረጉላት የመዋቢያ ቁሶች ጋር የሙያ ቁሳቁሶች (ምላጭ፣ ወስፌ፣ ጥጥና እንዝርት) ይደረጋል። እነዚህም ቁሳቁሶች በመህበረሰቡ የሴት ሚና የሆኑት ስፌት እና ፈትል እንደሚጠብቋት አመላካች ናቸው። እንዲሁም በእንግድነቷ ከአማቶቿ ምንም ነገር እንዳትጠይቅ፣ ለሙሽርነት ጊዜዋ የሚያስፈልጓትን ሁሉንም ቁሳቁሶች አሟልቶ መላክ ያስፈልጋል። ምክንያቱም በጫጉላ ቤት ቆይታዋ መነጋገር ስለማይፈቀድ እንደሆነ ይነገራል። ይህም አንድም ከማክበር ሌላም በመነጋገር ሂደት የቋንቋ አጠቃቀም ስህተት ልትፈጽምና መሳቂያ መሳለቂያ ልትሆን ትችላለች ከሚል ጥንቃቄ ነው። ቀደም ባለው ጊዜ የጫጉላ ቤት ቆይታ ለሁለት ወራት ያህል እንደነበርና በቆይታዋም ሙሽሪት ፈትላ ያሰራችውን ጋቢ እና ነጠላ ለአማቶቿ የጫጉላ ግላጭ ስጦታ እንደምትሰጥ፣ ከዚህም ባሻገር በተለያዩ ሙያዎች ስትፈተን እንደምትቆይ ይነገራል። የግላጯ ዕለት ወደ ማህበረሰቡ ስትቀላቀል የሰፋችው ስፌትና የፈተለችው ፈትል እየታየ ትመረቃለች፣ በዘፈንም ትሞገሳለች (ወ/ሮ ቦሰና፣ 12/06/2012 ዓ.ም የተካሄደ ቃለ መጠይቅ)።

ሙሽሪትማ የፈተለችው፣
የሸረሪት ድር አስመሰለችው፣
ሸማኔ ጠፍቶ ማሪያም ሰራችው።

ተብላ ትወደሳለች።

ባጠቃላይ የጋብቻ ሥርዓት ክዋኔዎች ተጋቢዎች ከሽግግሩ በኋላ የሚቀላቀሉበትን ግላዊና ማህበራዊ ደረጃ የማስተዋወቅ ሚናው የጎላ ነው። በዚህም ሙሽሮች ፈጽሞ ወደማያውቁት አዲስ ዓለም ገብተው ከመደናበራቸው በፊት ፍንጭ እንዲያገኙና ለለውጡ ዝግጅት እንዲያደርጉና ለውጡን እንዲያካሂዱ ይረዳቸዋል። በሽግግሩ የሚደርሱበት ደረጃም ማህበራዊ ሲሆን ጋብቻ ደግሞ ለባለትዳርነት ወይም ለህጋዊ ሚስትነት/ባልነት ደረጃ ያሸጋግራል። የጋብቻ ሥርዓት ለአካለ መጠን መብቃትን ያውጃል።

## 3.7. የማህበረሰቡን የእርስበርስ ትስስር ማጠንከር

በጃቢ ጠህናን ወረዳ ጋብቻ አንዱና ዋናው የዝምድና መፍጠሪያ ዘዴ ሲሆን በቡድን የሚከናወኑ ሥነ ሥርዓቶችም የማህበረሰቡን የእርስበርስ ትስስር ያጠነክራሉ። ጋብቻ ጠበቅ ያለና ወሳኝ ሽግግር በመሆኑ ውጤቱ ምን ይሆን በሚለው ዙሪያ ባለጉዳዩንም ሆነ ማህበረሰቡን ያሳስባሉ። እንደ ዋና መገናኛ፣ እሴቱን ማጠንከሪያና ማስጠበቂያ በመሆኑ ሽግግሩና የደረጃ ለውጡ ከባለጉዳዩ አልፎ የማህበረሰቡን ህልውና ያስቀጥላል። በመሆኑም በጋብቻ ሥነ ሥርዓት ማህበረሰቡ በጉልበትም ሆነ በሃሳብ ይረዳዳል። ዋና ቤተሰቦችን አይዟችሁ፣ እየተሟላ ነው፣ ምን ጎደለ ብሎ ከመጠየቅ ጀምሮ የሚበላና የሚጠጣ አቀልቋይ[24] በመሾም፣ ጠላ ሲደረግ በማገዝ፣ ደረቆት በመቁላት፣ ዳስ በመጣል፣ ፍሪዳ በማረድ፣ እንግዳ በማስተናገድ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ አብሮነቱን ያሳያል (አቶ እንዳለው፣ 05/05/2012 ዓ.ም የተካሄደ ቃለ መጠይቅ)። ይህም የማህበረሰቡን የእርስ በርስ ትስስር የማጠንከር ሚናው የጎላ መሆንን ያመለክታል።

## 4. መደምደሚያ

ባጠቃላይ በዚህ ጥናት ከሰርግ ዋዜማ እስከ ጫጉላ ግላጭ ድረስ የሚፈጸሙ የጋብቻ ሽግግር ሥርዓት ክዋኔዎችን ምንነትና ለሙሽሮችም ሆነ ለማህበረሰቡ ያላቸውን ሚና አሳይቷል፡፡ ምሪ የመፍታት ሥነ ሥርዓት ሙሽሪትን ለጋብቻውና ከጋብቻው በኋላ ስለሚጠብቋት ግላዊና ማህበራዊ ሚናዎች መረጃ በመስጠት የቅድመ ጋብቻ ዝግጅት እንድታደርግ ይረዳታል። ጥያቄ የመጠየቅና ቃል የማስገባት ሥነ ሥርዓቶችም ሙሽሪት ሚዜዎችን ቀድማ እንድታውቃቸው የሚረዳት አጋጣሚ ነው። ለቤተሰቡ ደግሞ ልጃቸውን አምነው ለመስጠት ከሙሽራው ጋር ያላቸውን የስጋ ዝምድና ማወቃቸው እምነትንና መረጋጋትን ይፈጥርላቸዋል። ዙረሽ ግቢ ሙሽሪት መለየትን (መነጠልን) የምትለማመድበት፣ ከሙሽራውም ሆነ ከሚዜዎቹ ጋር መጠነኛ ትውውቅ የምታደርግበት አጋጣሚ በመሆኑ ሚናው የጎላ ነው። ከዚያም በጫጉላ ቤት ቆይታቸው የተለየ ምግብ ይመገባሉ። በጫጉላ ቤት ያለውን ቆይታ ለመገምገም፣ ሙሽራ ጠያቂ ይላካል። በመጨረሻም እንደ ሽግግር ወቅት የሚታየው የሙሽርነት ጊዜ አብቅቶ በአዲስ ማንነት ወደ ማህበረሰቡ የምትቀላቀለው በጫጉላ ግላጭ ሥነ ሥርዓት መሆኑን ማጤን

24 የምግብና የመጠጥ እገዛ ማድረግ

ተችሏል። እነዚህ በተከታታይ የሚፈጸሙ ሥርዓተ ክዋኔዎች ሙሽሮችን ለጋብቻው ከማዘጋጀት ጀምሮ የሽግግር ወቅቱን በማጀብ፣ ህክምና በመስጠት፣ ለውጡን በማወጅና በማረጋገጥ፣ የማህበረሰቡን አብሮነት፣ የእርስበርስ መስተጋብር በማጎልበት ጉልህ ሚና ይጫወታሉ፡፡

ከጥናቱ የመረጃ ትንተና እና የማጠቃለያ ሀሳብ በመነሳት የሚከተሉት የይሁንታ ሀሳቦች ተጠቁመዋል፡፡

- የጋብቻ ሽግግር ስርዓተ ክዋኔዎች በዘመናዊው ጋብቻ ወቅት እንዲፈጸሙ በማድረግ ባህሉንና እውቀቱን ለማሳደግ ጥረት ቢደረግ፤
- ሀገር በቀል የሆኑ ማህበረሰባዊ እውቀቶችና ባህላዊ ክንውኖች ትኩረት ቢሰጣቸውና የመፍትሔ አካል የሚሆኑበት መንገድ ቢበረታታ፤
- ማህበረሰቡ በህይወቱ የሚያጋጥሙትን የማይስማሙ የሚመስሉ ተቃርኖዎችን አስማምቶ የሚያስቀጥልባቸው ብልሃቶች ከተለያዩ የትምህርት ዘርፎች (ከታሪክ፣ ከህግ፣ ከቋንቋ፣ ከፎክሎር፣ ከስነ ማህበረሰብና ከሌሎች) አንጻር ተጠንተው እንዲጎለብቱ ቢሰራ የሚሉት ይጠቀሳሉ፡፡

**ዋቢ ስራ**


Bell, Cathrine. (1997). *Ritual Perspectives and Dimensions*. New York: Oxford University Press.

Brana-Shute, R. and Brana-Shute G. (1979). Death in the Family: Ritual Therapy in a Creole Community. *Bijdragen tot de Taal-, Land- en Volkenkunde* 135(1): 59–85.

Canda, Edward. R. (1988). Therapeutic Transformation in Ritual, Therapy, and Human Development. *Journal of Religion and Health*, 27(3): 205-220.

Mazama, A. and Asante. M., Eds. (2009). *Encyclopedia of African Religion*. Thousand Oaks, CA: Sage Publications.

Pentkainen, J. (1979). The Symbolism of Liminality. *Scripta Instituti Donneriani Aboensis*, 10:154-166.

Salamone, Frank A., ed. (2004). *Encyclopedia of Rites, Rituals and Festivals.* London: Routledge New York.

Segal, Robert A., ed. (2006). *The Blackwell Companion to the Study of Religion*. Blackwell Publishing Ltd.

St. John, Graham (Ed.). (2008). *Victor Turner and Contemporary Cultural Performance.* New York and Oxford: Berghahn Books.

Turner, Victor. (1969). *The Ritual Process Structure and Anti-structure.* Itaca New York. Cornell University Press.

Turner, Victor. (1968). *The Forest of Symbols፡ Aspects of Ndembu Ritual*. United States of America Cornell Universty Press,

Van Gennep, A. (1960). *The Rites of Passage* (M.B. Vizedom & G.L. Caffee, Trans.). London: Routledge & Kegan Paul.